# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ

# ኤጀንሲ ስር በልዩ ልዩ

# የህብረት ስራ ማህበር ለሚደራጁ የአደረጃጀት መመሪያ ቁጥር 123/2014

የህብረት ስራ ማህበራት ሀገራችን ከያዘችው የልማትና የብልፅግና ጉዞ አንጻር እያበረከቱት የሚገኘው አስተዋፅኦ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረት ስራ ኤጀንሲ ቀደም ሲል በተለያዩ የህብረት ስራ ማህበራት ዓይነቶች ተደራጅተው የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገኙ በመሆኑ፤

በዚህም መሰረት በአገልግሎት፤በማምረት እና በማምረት እና በአገልግሎት ዘርፍ በመደረጃት እራሳቸውን፤ ቤተሰባቸውን እና ሀገራቸውን እየጠቀሙ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም በማምረት እና አገልግሎት በመስጠት ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ የህብረት ስራ ማህበራት ህግ እና መመሪያ አክብረው እንዲሰሩ ለማድረግ  በተለያዩ የህብረት ስራ ማህበራት ዓይነቶችና የሙያ ዘርፎች በማደራጀት እንዲሁም መብታቸውን በመጠቀም ህግን መሰረት አድርጎ መስራት የሚያስችል ይህ የአደረጃጀት መመሪያ መዘጋጀት በማስፈለጉ፤
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ኤጀንሲ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀፅ (3) ተራ ፊደል (ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ኤጀንሲ ስር በልዩ ልዩ የህብረት ስራ ማህበር ለሚደራጁ የአደረጃጀት መመሪያ ቁጥር-123/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

   በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

   1. **"አዋጅ"** ማለት የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 ማለት ነው፤
   2. **"ህብረት ስራ ማኅበር"** ማለት ቀደም ሲል በነበሩ አዋጆችና በአዋጅ ቁጥር 985/2009 የተደራጁና የተመዘገቡ ህብረት ሥራ ማኅበራት ማለት ነው፤
   3. **"ልዩ ልዩ ህብረት ስራ ማህበር"** ማለት በተለያዩ የህብረት ስራ ማህበራት ዓይነቶች የሚደራጁ ነው፤
   4. **"የሙያ ህብረት ስራ ማህበር"** ማለት የተለያዩ ሙያን መሰረት በማድረግ የሚደራጁ የህብረት ስራ ማህበራት ነው፤
   5. **"አግባብ ያለው ባለስልጣን"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማደራጀት፣ ለመመዝገብ፣ ምርምር ለማድረግና ለሌሎች ቴክኒካል ጉዳዮች ድጋፍ ለመስጠት ከህብረት ስራ ኤጀንሲ እስከ ወረዳ የተቋቋሙ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ጽህፈት ቤት ነው፡፤
   6. **"ልዩ ውሳኔ"** ማለት በህብረት ስራ ማህበሩ አባላት ላይ አስገዳጅነት እንዲኖረው በሁለት ሶስተኛው መፅደቅ ያለበት ውሳኔ ነው፤
   7. **"ጠቅላላ ጉባዔ"** ማለት የአንድ መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበር ግለሰብ አባላት ወይም ተወካዮቻቸው ወይም ከመሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበር የኅብረት ሥራ ማኅበር በላይ ከሆነ የመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት፣የህብረት ስራ ማህበራት ዩኒየኖች ወይም የህብረት ስራ ፌደሬሽኖች ተወካዮች የሚገኙበት ጉባኤ ነው፤
   8. **"አባል"** ማለት በህብረት ስራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት እንደ ህብረት ስራ ማህበሩ አይነት የተደነገጉትን የአባልነት መመዘኛወችን በማሟላት ለአባልነት ጥያቄ አቅርቦ ተቀባይነት ያገኘ ግለሰብ ወይም መሰረታዊ ማህበር ወይም የህብረት ስራ ማህበራት ዩኒየን ወይም የህብረት ስራ ማህበራት ፌደሬሽን ነው፤

9. **"ተወካይ"** ማለት አወካከሉ በህብረት ስራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ሆኖ በመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበር በግለሰብ አባላት ተወክሎ በጠቅላላ ጉባኤ ላይ ድምጽ የሚሰጥ ወይም በዩኒየንና በፌደሬሽን በጠቅላላ ጉባኤ ተመርጦ የህብረት ስራ ማህበራትን ተክቶ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ በመገኘት ድምጽ የሚሰጥ ግለሰብ ነው፤

10. **"መተዳደሪያ ደንብ"** ማለት የህብረት ስራ ማህበሩ የሚተዳደርበትን ዝርዝር ሁኔታ አሟልቶ የያዘና አግባብ ባለው አካል የተመዘገባና በየጊዜው የሚሻሻለውን ጨምሮ በጠቅላላ ጉባኤ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ የጸደቀ የህብረት ስራ ማህበሩ የሚተዳደርበት ህግ ነው፤

11. **"ስራ አመራር ኮሚቴ"** ማለት በጠቅላላ ጉባኤ ተመርጦ የአንድን ህብረት ስራ ማህበር ስራ እንዲመራ ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፤

12. **"ስራ አስኪያጅ"** ማለት ተጠሪነቱ ለህብረት ስራ አመራር ኮሚቴ የሆነና በተሰጠው ኃላፊነትና ስልጣን ገደብ መሰረት የህብረት ስራ ማህበሩን የዕለት ተዕለት ተግባራት የሚያከናውን ነው፤

13. **"ሰራተኛ"** ማለት ከአሰሪው ህብረት ስራ ማህበር ጋር በገባው ውል መሰረት የዕለት ከዕለት ስራዎችን እንዲያካሂድ በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ነው፤

14. **"መጠባበቂያ ሂሳብ"** ማለት ከዓመታዊ ትርፍ በህጉ መሰረት ለመጠባበቂያነት የሚያስቀምጠውና ለአባላት በትርፍ ድርሻነት የማይከፋፈል ሂሳብ ነው፤

15. **"ካፒታል"** ማለት የህብረት ስራ ማህበሩ ካለው ጠቅላላ ሀብት ላይ እዳው ተቀንሶ የሚገኝ ቀሪ የሀብት መጠን ነው፤

16. **"የህብረት ስራ ማህበራት ፈንድ"** ማለት ማንኛወም የህብረት ስራ ማህበር ለተለያዩ የጋር ጥቅሞች አገልግሎት ላይ የሚያውለው የጋር ንብረትና ገንዘብ ሆኖ ህብረት ስራ ማህበራቱ ህልውናቸውን በሚያጡበት ጊዜ የማይከፋፈል ሀብት ነው፤

17. **"የዕጣ ክፍያ"** ማለት በህብረት ስራ ማህበሩ የታወጀ ዋጋ ያለውና ለአባልነት እንደ መጀመሪያ ቅድመ ሁኔታ በጥሬ ገንዘብ ወይም በአይነት የተሸጠ ወይም የሚሸጥ ነው፤

18. **"ውህደት"** ማለት በንብረት ባለቤትነት ፣ በአስተዳደር ፣ በሥራ አካባቢ ፣ በስያሜ እና በተግባር፣የተለያዩና ህጋዊ ሰውነት የነበራቸውን ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ህብረት ስራ ማኅበራት አንድ ጠንካራ ህብረት ስራ ማኅበር ለመመስረት የሚያደርጉት መቀላቀል ውህደት ነዉ፤

19. “**የኅብረት ሥራ ማኅበራት መከፈል**” ማለት በንብረት ባለቤትነት፤ በአስተዳደር፤ በስራ አካባቢ፤ በስያሜ፤ በተግባር አንድ የህጋዊ ሰውነት የነበረውን ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወደ ሆኑ የህብረት ስራ ማህበራት በመከፈል የአባላትን ፍላጎት እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና ተደራሽ ለማድረግ ነው፤

20. "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. <u>የጾታ አገላለጽ</u>

በዚህ መመሪያ ዉስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

4. <u>**የመመሪያው ዓላማ**</u>

1. በተለያዩ የህብረት ስራ ማህበራት ዓይነቶች ለመደረጀት ፍላጎት ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ችግሮቻቸውን ለማቃለል፣
2. የህብረት ስራ ማህበራት የአደረጃጀትና የአሰራር ስርዓትን ተከትለው እንዲደራጁና እንዲሰሩ ለማድረግ፣
3. በተለያዩ የህብረት ስራ ማህበራት የአካል ጉዳተኞችን፣ ሴቶችንና ወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማጎልበት፣
4. በተለያየ የሙያ ዘርፍ ተመርቀው በህብረት ስራ ማህበራት ለመደራጀት ፍላጎት ያለቸውን ማደረጀት ነዉ፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የኅብረት ሥራ ማኅበራት አመሠራረት እና የአመሠራረት ሂደት</u>

5. <u>**አመሠራረት**</u>

1. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከመሠረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት ጀምሮ እስከ ፌደሬሽን ሊደራጁ ይችላሉ፡፡
2. የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ሲመሠረቱ በአንድ በተወሰነ የመኖሪያ ወይም የሥራ ክልል የሚኖሩ እና በተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ የተሰማሩና ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸው ሆኖ የአባላት ብዛት እንደየ የህብረት ስራ ማህበሩ የአደረጃጀት መነሻ ቁጥር ይሆናል፡፡

| | የህብረት ስራ ማህበሩ ዓይነት | መነሻ ቁጥር |
|---|---|---|
| | **የሸማቾች ኃላ/የተ/ የህብረት ስራ ማህበር** | 250 |
| | **የግንባታና ኮንስትራክሽን ጥሬ ዕቃና ውጤቶች አምራቾች ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር** | 50 |
| | ▪ የግንባታና ኮንስትራክሽን አምራቾች ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 50 |
| | **የኢንደስትሪና ዕደ-ጥበብ ውጤቶች አምራቾች ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህብር** | 25 |
| | ▪ የሽመና ውጤቶች አምራቾች ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 25 |
| | ▪ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች አምራቾች ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 25 |
| | ▪ የሸክላና ሸክላ አምራቾች ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 25 |
| | ▪ የሳሙናና የጽዳት ዕቃዎች አምራቾች ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 25 |
| | ▪ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች አምራቾች ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 25 |
| | ▪ የመነጽር አምራቾች ኃላ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር | 25 |
| | ▪ የልብስ ስፌት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 25 |
| | **የጽዳት ውበት ኃ/የተ/ የህብረት ስራ ማህበር** | 12 |
| | ▪ የቆሻሻ ማንሳት አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 12 |
| | ▪ የመኪና እጥበት አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 12 |
| | ▪ የቤቶችና ግቢ ጽዳት አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 12 |
| | ▪ የጽዳትና የሻወር አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 12 |
| | **የባልትና ውጤቶች አምራቾች ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር** | 50 |
| | **የምግብ ዝግጅት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር** | 50 |
| | **የጫኝና አውራጅ አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር** | 50 |
| | **የትራንስፖርት አገልግሎት ኃላ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር** | 100 |
| | **እንስሳትና እንስሳት ተዋጽኦ አምራቾች ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር** | 50 |
| | ወተትና ወተት ተዋጽኦ ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 50 |
| | ዶሮ እርባታ ኃ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 50 |
| | **የሙያ አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር** | 12 |
| ▪ | የጤና ሙያ አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 12 |
| ▪ | የሂሳብ አዋቂዎች አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 12 |
| ▪ | የትምህርትና ስልጠና ባለሙያዎች አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 12 |
| ▪ | የኤሌክትሪክ ባለሙያዎች አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 12 |
| ▪ | የምህንድስና ባለሙያዎች አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 12 |
| ▪ | የማማከር አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 12 |
| ▪ | ግንበኖችና አናፂዎች አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 12 |
| ▪ | የቱሪዝም አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር | 12 |

3. የህብረት ስራ ማኅበሩ አባላት በግል በመንቀሳቀስ ሊያገኙት የማይችሉትን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ለማግኘት በፍቃደኝነት አባል የሚሆኑበትና የሚመሠርቱት ህብረት ስራ ማኅበር ሆኖ አባላት ሊያገኙት ከሚፈልጉት ጥቅም አንፃር ሊደራጁ ይችላሉ፤

4. የኅብረት ሥራ ማኅበሩ የአባላትን ፍላጎት ለማርካት በሚያደርገው አደረጃጀት በንግድ ሥራ ዕቅዱ መሠረት ተግባራዊ ሊያደርግ የሚፈልገውን የሥራ ዘርፍ መፈፀም ይችል ዘንድ የአባላትን አቅም ያገናዘበ የመነሻ ካፒታል ያስፈልገዋል፡፡

5. ኤጀንሲዉ የህብረት ስራ ማኅበሩን ጥናት መሠረት በማድረግ የሚሰጠውን አገልግሎት መወሰን ይችላል፡፡

6. በዚህ መመሪያ መሰረት በሚደራጁ የህብረት ስራ ማህበራት የሙያ ብቃት በሚጠይቁ የህብረት ስራ ማህበራት ዓይነቶች ላይ ሁሉም አባላት በተናጠል ከሚመለከተው አካል ላይ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 7. <u>የአመሠራረት ሂደት</u>

1. የኅብረት ሥራ ማኅበራት በራሳቸዉ ተነሳሽነት ወይም በባለሙያዎች አማካይነት በተፈጠረ ግንዛቤ የተለያዩ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ሊመሠራቱ የሚችሉ ሲሆን የህብረት ስራ ማህበሩ ዓይነት እና መነሻ ቁጥር በሰንተረዝው መሰረት ይሆናል፡፡

2. የህብረት ስራ ማህበራት ሲመሰረቱ ከዚህ በታች ያሉትን የአሠራር ቅደም ተከተል ተግባራዊ መደረግ ይኖርባቸዋል፡-

   ሀ) የአካባቢውን ባሕላዊ፣ ማኅበራዊና ኦኮኖሚያዊ ሁኔታዎች መቃኘት፣

   ለ) ለህብረተሰቡ በባለሙያዎች እና በአካባቢው ተቀባይነት ባላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ እንዲፈጠር ማድረግ፣

   ሐ) የመስራች ኮሚቴ እንዲቋቋም ማድረግ፣ የመስራች ኮሚቴው ሰብሳቢ፣ ፀሐፊ እና ገንዘብ ያዥ ይኖረዋል፡፡

## 8. <u>የህብረት ስራ ማህበራት ሰነዶች</u>

1. የህብረት ስራ ማህበራት ማቋቋሚያ ሰነድ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

   ሀ) የመስራቾች ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ እና የአባላት ፊርማ፤

   ለ) የህብረት ስራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ዋና እና ሌሎች ሁለት ቅጅ፤

ሐ) የህብረት ስራ ማህበሩ የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት ስም፣የስራ ድርሻ፣ሀላፊነት ፤አድራሻ እና ፊርማ፤

መ) የህብረት ስራ ማህበሩ የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ስም፤ሀላፊነት አድራሻ እና ፊረማ፤

ሠ) የህብረት ስራ አባላት ሆነው የሚመዘገቡ ግለሰቦች አባል ለመሆን ብቁ መሆናቸውን የሚያስረዱ ዝርዝር ሁኔታዎች በህብረት ስራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በግልፅ መቀመጡን ማረጋገጥ፤

ረ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በላይ ከሆነ አባል የሚሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት ተመሳሳይ ዓላማ እና ተግባር እንዲሁም ፍላጎት ያላቸው ስለመሆኑ፤

ሰ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በላይ ከሆነ የመስራች አባል ኅብረት ሥራ ማህበራትን አድራሻ እና የተወካዮች ፊርማ መያዝ አለበት፤

ሸ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሦስት ዓመት የሥራ ዕቅድ፤

ቀ) የመነሻ ካፒታሉን መጠንና ተሰብስቦ በባንክ ሂሳብ ገቢ መደረጉን የሚያረጋግጥ ሰነድ፤

በ) ኅብረት ሥራ ማኅበሩ የሚሠራበት ቦታ ወይም ጽ/ቤት መግለጫ፤

ተ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የአዋጭነት ጥናት፤

2. ለመደራጀት የሚመጣው የህብረት ስራ ማህበር ከላይ በዝርዝር የተቀመጡ መስፈርቶችን አሟልቶ ሲቀርብ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የቀረበለትን የምዝገባ ማመልከቻ መርምሮ የተሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥ በአምስት(5) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበሩን መዝግቦ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤
3. በዚህም የምዝገባ ምስክር ወረቀት ላይ ህብረት ስራ ማኅበሩ የተመዘገበበት ቀን በመተዳደሪያ ደንቡ የመጨረሻው አንቀፅ ላይ ይጠቀሳል፤
4. አግባብ ያለው ባለሥልጣን አመልካቹን ህብረት ስራ ማህበር መመዝገብ አይገባውም ሲል የወሰነ እንደ ሆነ ምክንያቱን በጽሑፍ በማድረግ ለህብረት ስራ ማህበሩ ወኪሎች በአምስት(5) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ መግለፅ አለበት፡፡

9. <u>የምዝገባ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ጥያቄ አቀራረብ</u>

1. በዚህ መመሪያ መሰረት መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በወረዳ ይመዘገባሉ፣
2. በልዩ ባህሪያቸው ምክንያት በአንድ ወረዳ መደራጀት የማይችሉትን ክፍለ ከተማ ይመዘግባቸዋል፤

3. በልዩ ባህሪያቸው ምክንያት በአንድ ክፍለ ከተማ መደራጀት የማይችሉት ከሆነ ደግሞ በከተማ አስተዳደሩ የህብረት ስራ ኤጀንሲ አማካኝነት ይመዘገባሉ፣
4. የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩን ወይም ፌዴሬሽን በማዕከል ይመዘገባል፡፡ ሆኖም አስፈላጊነቱ በኤጀንሲው ከታመነበት ዩኒዩን በክፍለ ከተማ ደረጃ ሊመዘገብ ይችላል፡፡

10.<u>**የምዝገባ የምስክር ወረቀት የሚይዛቸው ዝርዝሮች**</u>

የምዝገባ የምስክር ወረቀት በከተማ አስተዳደሩ ህብረት ስራ አጀንሲ የሚታተም ሆኖ መያዝ ያለበት፡-

1. የምዝገባ ቁጥር፣ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም፣ ሙሉ አድራሻ እና አርማ፣
2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ የተመዘገበበት የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር፣ ቀን እና ዓመተ ምህረት፣
3. የኅብረት ሥራ ማህበሩን የመዘገበው አግባብ ያለው ባለሥልጣን ፊርማ፣
4. የመዝጋቢው ባለሥልጣን መስሪያ ቤት ማህተም፣
5. የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት፣

6 የታደሰበት ቀን፣ ወር፣ ዓመተ ምህረት እና ያደሰው ባለሥልጣን ፊርማ፡፡

11.<u>**የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማገድ**</u>

ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ከተቋቋመበት ዓላማና መርህ ውጪ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ የተፈቀደለትን ሥራ እንዳይሠራ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሊያግድ ይችላል፡፡

12.<u>**በማገድ የሚወሰዱ እርምጃዎች**</u>

1. በኢንስፔክሽን ሪፖርት መሰረት ጥፋቱ የሚያሳግድ ሆኖ ሲገኝ ኢንስፔክት ያደረገው አግባብ ባለው ባለስልጣን የኢንስፔክሽን ባለሙያ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ኢንስፔክት እንደተደረገ ከስራ ያግዳል፤
2. አግባብ ያለው ባለስልጣን የተሰጠውን የእግድ ውሳኔ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፤ የታገደው ኅብረት ሥራ ማህበር ዕግዱ እንዲነሳለት በ30 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ካላመለከተ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሕጋዊ የማፍረስ እርምጃ ይወስዳል፤
3. የታገደ ኅብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ዕግዱ እንዲነሳለት አግባብ ላለው ባለሥልጣን ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፤
4. ጥያቄውን የተቀበለው አግባብ ያለው ባለሥልጣን የህብረት ስራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እግዱ እንዲነሳለት ያቀረበው ምክንያት በቂና አግባብ ሆኖ ሲገኝ እግዱን ሊያነሳ ይችላል፤

5. አግባብ ያለው ባለሥልጣን እግዱን ያላነሳ እንደሆነ ያላነሳበትን ምክንያት በጽሑፍ ያሳውቃል፤

6. አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ አካል የዳኝነት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

13.<u>ምትክ የምዝገባ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ</u>

1. የምትክ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ጥያቄ የሚቀርበው የምስክር ወረቀቱ ሲጠፋ፣ ሲበላሽ እና የስም ለውጥ ሲደረግ ይሆናል፤
2. የምትክ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ሲቀርብ ከዚህ በታች ያሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፡-

   ሀ) የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የጠፋ ስለመሆኑ በፍትህ አካላት ሲረጋገጥ፤

   ለ) የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የተበላሸ ከሆነ እና የተበላሸው የምስክር ወረቀት አግባብ ላለው ባለስልጠን ቀርቦ ሲረጋገጥ፤

   ሐ) የምትክ ህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጥያቄ ያቀረበው የኅብረት ሥራ ማህበር የስም ለውጥ ያደረገ ከሆነ እና የስም ለውጡ የተፈቀደበት የፍርድ ቤት ማስረጃ እና የኅብረት ሥራ ማህበሩ የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ.ጉባኤ የስም ለውጡን አሰመልክቶ ያስተላለፈውን ውሳኔ እና የሥራ አመራር ኮሚቴ በደብዳቤ አረጋግጦ ማመልከቻ ሲያቀርብ፤

   መ) የስም ለውጡ ተቀባይነት የሚያገኘው የምትክ ምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ምዝገባ የሚያካሂደው አግባብ ያለው ባለሥልጣን የኅብረት ሥራ ማህበሩ ማህተም፤ መተዳደሪያ ደንብ፣ ሰነዶች እና ሌሎች የቀድሞ ስም ያለባቸው በሙሉ በአዲስ ስም መለወጣቸውን እና መመለሳቸውን አግባብ ያለው ባለስልጣን ሲረጋግጥ፤

   ሠ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማግኘት የሚችለው አስፈላጊውን ክፍያ ፈጽሞ አግባብ ላለው ባለስልጣን ደረሰኝ ሲያቀርብ እና ቀደም ሲል በመዝገብ ላይ ባለው የቀድሞ ቁጥር ሲመዘግብ ነው፡፡

14.<u>ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ እና አመላለስ</u>

1. ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ፡-

   ሀ) ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚሰጠው ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ብቻ ይሆናል፤

ለ) ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚሰጠው ኅብረት ሥራ ማኅበሩ የሚሠራበት ቦታ ወይም ጽህፈት ቤት መግለጫ እና በሌሎች መመሪያዎች የሚወሰኑ መግለጫዎችን ባያሟላም እስከሚያሟላ ድረስ ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ሊያገኝ ይችላል፤

ሐ) ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያገኘ ኅብረት ሥራ ማህበር በተመዘገበበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ያለው መብት እና ግዴታ ይኖረዋል፡፡

2. ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚመለሰው የመከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ይሆናል፡-

ሀ) ኅብረት ስራ ማህበሩ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መስፈርቶችን ሙሉ ለሙሉ አሟልቶ ሲገኝ ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን እንዲመልስ በማድረግ ተገቢውን ክፍያ ፈጽሞ አዲስ ቋሚ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤

ለ) ኅብረት ሥራ ማህበሩ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መስፈርቶቹን የማያሟላ ከሆነ በህጋዊ መንገድ ለማፍረስ ስልጣን የተሰጠዉ አግብብ ያለው ባለስልጣን የኅብረት ሥራ ማህበሩን የማፍረስ ተግባር ተፈፃሚ ያደርጋል፡፡

15. <u>የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለማሳደስ</u>

1. ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በየሦስት ዓመቱ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን የማሳደስ ግዴታ አለበት፤

2. የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማሳደስ የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡-

ሀ) ከቅርብ አደራጅ መስሪያ ቤት ጉዳዩ ከሚመለከተው ክፍል ባለፉት ሦስት ዓመታት ኅብረት ስራ ማህበሩ በተቋቋመበት ዓላማ መሰረት እየሠራ ስለመሆኑ፣ የአባላት ተሳትፎ መኖሩን ፣ ለአባላት እየሰጠ ያለው አገልግሎት እና ጥቅም አጭር መግለጫ ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀው ፎርም ላይ በመሙላት ያቀርባል፤

ለ) በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የዘመኑ የኦዲት ሪፖርት፤

ሐ) የብቃት ደረጃ ማረጋገጫና ዕውቅና ሠርተፊኬት፤

3. በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ያላሳደሰ ኅብረት ሥራ ማህበር እንደታገደ የሚከተሉት እርምጃዎች ይወሰዳል፡-

ሀ) አግባብ ያለው ባለሥልጣን ኅብረት ሥራ ማህበሩ ያላሳደሰበትን ምክንያት በ30 ተከታታይ የስራ ቀን ውስጥ በጽሁፍ እንዲያቀርብ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ይሠጠዋል፤

ለ) በተወሰነው ጊዜ ውስጥ አጥጋቢ ምክንያት ካላቀረበ በሥራ አመራር ኮሚቴው አማካኝነት በ15 ቀን ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራ ይደረጋል፤

ሐ) የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ ጠቅላላ ጉባኤውን ካልጠራ አግብባ ያለው ባለስልጣን ጠቅላላ ጉባኤውን በመጥራት ውሳኔ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

መ) አግባብ ያለው ባለስልጣን በህጉ መሰረት ውሳኔ በመስጠት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

4. ከእገዳው በኋላ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያደረገው በህጉ መሠረት ህልውናውን እንዲያጣ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለሚደራጁ ማህበራት አይነቶች

### 16.የሚደራጁ የህብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች

1. የሸማቾች ኃ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር፤
2. የኢንዱስትሪና እደ-ጥበብ ውጤት አምራቾች ኃ/የተ/ ህበብረት ስራ ማህበር፤
3. የግንባታና ኮንስትራክሽን ትሬ ዕቃ ውቴቶች አምራቾች ኃ/የተ/ ህበብረት ስራ ማህበር፤
4. የጽዳትና ውበት አገልግሎት ሰጭ ኃ/የተ/ የህብረት ስራ ማህበር፤
5. የባልትና ውጤቶች አምራቾች ኃ/የተ/ የህብረት ስራ ማህበር፤
6. የምግብ ዝግጅት አገልግሎት ኃ/የተ/ የህብረት ስራ ማህበር፤
7. የልዩ ሙያ አገልግሎት ኃ/የተ/ የህብረት ስራ ማህበር፤
8. የጫኝና አውራጅ አገልግሎት ኃ/የተ/ የህብረት ስራ ማህበር፤
9. የትራንስፖርት አገልግሎት ኃ/የተ/ የህብረት ስራ ማህበር፤
10. የእንስሳትና እንስሰታ ተዋጽኦ ኃ/የተ/ የህብረት ስራ ማህበር፤

### 17.በተለያዩ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚደራጁ የህብረት ስራ ማህበራት ዓላማና ተግባር

**1. የሸማቾች ኃላ/የተ/የህብረት ስራ ማህበር ዓላማ**

ሀ) ለህብረት ስራ ማህበሩ አባላት መሰረታዊ ፍላጎቶችን ወይም ልዩ ልዩ ምርቶችን በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብ ማድርግ፤

ለ) የፍጆታ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን ለአባላት በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ ማድረግ፤

ሐ) አባል ለሆኑ እና ላልሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ልዩ ልዩ የድጎማ ምርቶችን ለተጠቃሚው እንዲቀርብ ማድረግ፤

መ) ለህብረት ስራ ማህበሩ አባላት ልዩ ልዩ ምርቶችን በአባላት መኖሪያ አካባቢ እንዲቀርብ ማድረግ፤

ሠ) የህብረት ስራ ማህበሩ አባላት ባላቸው የዕጣ እና የተሳትፎ መጠን የትርፍ ክፍፍል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤

ረ) ለህብረት ስራ ማህበሩ አባላት ጥሬ ምርቶች እሴት ተጨምሮባቸው እንዲቀርቡ ማድረግ ናቸዉ፡፡

2. **የሸማቾች ኃላ/የተ/የህብረት ስራ ማህበር ተግባር**

ሀ) የአባላትን መሰረታዊ ፍላጎቶች መሰረት በማደረግ አመቺ በሆነ ቦታ ሱቆችን የመሸጫ በመገንባት ለአባላት አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ፤

ለ) ለፍጆታ የሚውሉ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን በጥራት፤በተመጣጣኝ ዋጋ እና በበቂ መጠን ለአባላት ማቅረብ፤

ሐ) የቀረቡ ምርቶች እንዳይባክኑ እና እንዳይበላሹ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፤

መ) አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፤

ሠ) የህብረት ስራ ማህበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ በትክክትል መፈፀም እንዲችል የተለያዩ የአሰራር መመሪያዎችን ማዘጋጀት፤

ረ) ለልዩ ልዩ ኮሚቴዎች፤ለአባላት፤ለቅጥር ሰራተኞች እና ለአካባቢው ህብረተሰብ ተከታታይነት ያለው ትምህረትና ስልጠና መስጠት፤

ሰ) አባላት ከህብረት ስራ ማህበራቸው ጋር የሚያደርጉትን ማንኛውንም እንቅስቃሴ በአባላት የተሳትፎ ካርድ እና መዝገብ ላይ መመዝገብ፤

ሸ) የምርትና አገልግሎቶችን ጥራትና ደረጃ ለማሻሻል በመስኩ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማሰማራት፤

ቀ) የህብረት ስራ ማህበሩ ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ሌሎች ተመሳሳይ ስራዎችን ማከናወን ናቸዉ፡፡

## 18.የሽመና ውጤቶች አምራቾች ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ

1. የህብረት ስራ ማህበሩ የሽመና ውጤቶችን በጥራትና በዘመናዊ መንገድ በማምረት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብ ማድርግ፤
2. የተለያዩ ዲዛይኖችን ተጠቅሞ በማምረት የሽመና ኢንዱስትሪው የአገሪቱን ባህል ፤እሴት እና ገፅታ እንዲጎለብት ማድረግ፤
3. የሽመና አሰራራቸውን በዘመናዊ ቴክኖሎጅ በመታገዝ የአባላትን ተጠቃሚነት እዲያድግ መስራት፤
4. ለአባላት ዘመናዊ የሽመና አመራረት ዘዴዎችን አስመልክቶ የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ፡፡

## 22.የሽመና ውጤቶች አምራቾች ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ተግባር

1. የህብረት ስራ ማህበሩ ባህላዊ ይዘታቸውን ሳይለቁ የሽመና ውጤቶችን በጥራትና በዘመናዊ መንገድ በማምረት በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚው ማቅረብ፤
2. በዘርፉ ያለውን የአመለካከት ችግር ለማስተካከል ቀጣይነት ያለው የሽመና ምርት እና አገልግሎት የማስተዋቅ ስራ መስራት፤
3. የህብረት ስራ ማህበሩ የሽመና ውጤቶችን ከባለድረሻ ካላት ጋር የተቀናጀ ተግባራትን ማከናወን፤
4. አዳዲስ አሰራረሮችን ተግባራዊ በማድረግ በዘርፉ ተወዳዳሪ መሆን፣
5. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
6. የተለያዩ ቴክኖሎጅዎችን ተጠቅሞ የሽመና ውጤቶችን ማምረት የሚችል እና አቅም ያለው አባል መፍጠር፣
7. የተለያዩ ዲዛይኖችን ተጠቅሞ በማምረት የሽመና ኢንዱስትሪው የአገሪቱን ባህል ፤እሴት እና ገፅታ እንዲያጎለብት መስራት፣
8. የሽመና አሰራራቸውን በዘመናዊ ቴክኖሎጅ በመታገዝ የአባላትን ተጠቃሚነት እዲያድግ መስራት፤
9. የሽመና ውጤቶች አምራቾች የህብረት ስራ ማህበሩ  የአባላት ተሳትፎ መዝገብ ላይ መመዝገብ፤
10. ለህብረት ስራ ማህበሩ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች፤ለአባላት እና ለቅጥር ሰራተኞች ተከታታይነት ያለው ትምህረትና ስልጠና መስጠት፤

11.የሽመና ውጤቶች አምራቾች የህብረት ስራ ማህበር ጥራት እና አሰራርን ለማሻሻል ተመሳሳይነት ያላቸው ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

23. <u>የቤትና የቢሮ ዕቃዎች አምራቾች ኃ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. የህብረት ስራ ማህበሩ የቢሮና የቤት ዕቃዎችን በማምረት ለተጠቃሚው በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብ ማድረግ፣
2. የህብረት ስራ ማህበሩ የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች የሚቀርቡበትን ስልት እንዲቀየስ ማድረግ፣
3. የህብረት ስራ ማህበሩ የሚያመርታቸውን የምርት ውጤቶች ላይ አዳዲስ ቴክኖሎጅ በመጠቀም ተወዳዳሪ የሚሆንበትን አሰራር መንደፍ፣
4. የህብረት ስራ ማህበሩ የአባላትን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት እንዲጎለብት ማድረግ፣
5. የህብረት ስራ ማህበሩ የአባላት ተሳትፎ የሚጎለብትበትን የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ፡፡

24.<u>የቤትና የቢሮ ዕቃዎች አምራቾች ኃ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. የህብረት ስራ ማህበሩ የአባላትን የማምረት አቅም ለማጎልበት የሚያስችል ስልጠና መስጠት፣
2. የቤትና የቢሮ ዕቃዎችን አዳዲስ ዲዛይኖችን በመጠቀም ተመራጭ የሚሆንበትን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣
3. ጥራት ያላቸውን የቤትና የቢሮ ዕቃዎችን በማምረት ለተጠቃሚው በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ፣
4. የህብረት ስራ ማህበሩ የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች የሚቀርቡበትን ስልት እንዲቀየስ ማድረግ፣
5. የህብረት ስራ ማህበሩ የአባላትን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት እንዲጎለብት መስራት፣
6. የህብረት ስራ ማህበሩ አባላትን ተሳትፎ በመዝገብ ላይ መመዝገብ፤
7. ለህብረት ስራ ማህበሩ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች፤ለአባላት እና ለቅጥር ሰራተኞች የቤትና የቢሮ ዕቃዎች አመራረትን አስመልክቶ ተከታታይነት ያለው ስልጠና መስጠት፤
8. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
9. የህብረት ስራ ማህበሩን አሰራር ለማሻሻል የሚያስችሉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል::

25.<u>የሸክላ አምራቾች ኃ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. የህብረት ስራ ማህበሩ ጥራት ያላቸውን የሸክላ ስራ ውጤቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ፣
2. የህብረት ስራ ማህበሩ የሚያመርታቸውን ምርቶች በአገር ውስጥና በውጭ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ፣
3. የተለያዩ የሸክላ ውጤቶችን በጥራት እና ባህላዊ እሴታቸውን ሳይለቁ በዘመናዊ መንገድ እንዲሰሩ ማደረግ፣
4. የህብረት ስራ ማህበሩ ህብረተሰቡ በሸክላ ስራ ዘርፍ ላይ ያለውን የተሳሳተ አመለካከት መቀነስ የሚያስችል ጥረት ማድረግ፣
5. የህብረት ስራ ማህበሩ በሚሰራቸው የሸክላ ውጤቶች ላይ ህብረተሰቡ የላቀ ግንዛቤ እንዲይዝ ማስተዋወቅ::

26.<u>የሸክላ አምራቾች ኃ/የተ/ህብረት ስራ ማህበርተግባር</u>

1. የተለያዩ የሸክላ ምርቶችን በማምረትና ለገበያ በማቅረብ የአባላትን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ፣
2. ባህላዊ የሸክላ ውጤቶችን በጥራትና ተገልጋዩ በሚፈለገው ዲዛይን መሰረት በማምረት ለተጠቃሚ ማቅረብ፣
3. በሸክላ ስራ የተሰማሩ አባላትን ልዩ ልዩ የክህሎት ስልጠናዎችን በመስጠት ውጤታማነታቸውን ማጎልበት፣
4. የህብረት ስራ ማህበሩን ዓላማ ለማሳካት ከሚያስችሉ አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት ውጤታማ ተግባራትን ማከናወን፣
5. የአባላትን ተሳትፎ በተሳትፎ መዝገብ ላይ መመዝገብ፣
6. ህብረት ስራ ማህበሩ የሸክላ ውጤቶቹን የማስተዋወቅ ስራ መስራት፣
7. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
8. ለማህበረሰቡ በሸክላ ስራ አስፈላጊነት ላይ ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ፈጠራ ስራ መስራት፣
9. የሸክላ ስራውን ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን::

27.<u>የሳሙናና የጽዳት ዕቃዎች አምራቾች ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. የህብረት ስራ ማህበሩ ጥራት ያላቸውን ለመፀዳጃ የሚያገለግሉ የሳሙና እና የፅዳት ዕቃዎችን በማምረት ለህብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብ ማድረግ፣

2. ከውጪ ይገቡ የነበሩ ዕዳት ዕቃዎችን በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ በማድርግ የውጭ ምንዛሬን እጥረት ለመቀነስ ጥረት ማድረግ፤
3. የህብረት ስራ ማህበሩ አባላት ልዩ ልዩ የዕዳት ዕቃዎችን በማምረት ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፤
4. የህብረት ስራ ማህበሩ የአባላት ተሳትፎ የሚጎለብትበት የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ፡፡

28. <u>የሳሙናና የጽዳት ዕቃዎች አምራቾች ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. የተለያዩ የፅዳት ዕቃዎችን በማምረትና ለገበያ በማቅረብ የአባላትን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ፣
2. የሳሙና ምርቶችን በጥራትና ተገልጋዩ በሚፈለገው መጠን በማምረት ለተጠቃሚ ማቅረብ፣
3. በሙያ ዘርፉ ለተሰማሩ አባላት ልዩ ልዩ የክህሎት ስልጠናዎችን በመስጠት ውጤታማነታቸውን ማጎልበት፣
4. ህብረት ስራ ማህበሩ ዓላማ ለማሳካት መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመቀናጀት ጥራት ያለው ምርት ማምረት፣
5. የአባላትን ተሳትፎ በተሳትፎ መዝገብ ላይ መመዝገብ፣
6. ህብረት ስራ ማህበሩ የሚያመርታቸውን የፅዳትና የሳሙና ምርቶች የማስተዋወቅ ስራ መስራት፣
7. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
8. የሳሙና እና የፅዳት ዕቃዎችን ስራ ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን::

29.<u>ቆዳና የቆዳ ውጤቶች አምራቾች ኃ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. የተለያዩ የቆዳ ውጤቶችን በጥራትና በተመጣጠኝ ዋጋ በማምርትና ለገበያ በማቅረብ የአባላትን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት እንዲጎለብት ማድረግ፣
2. የአባላትን ክህሎት በማሳደግ፣ በራስ መተማመን እንዲያዳብሩ ማስቻል፣
3. የተለያዩ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም፣ከመንግስትና ከአቻ ተቋማት ጋር ልምድ በመለዋወጥና በማሰልጠን የአባላትን የማምረት አቅምና ውጤታማነት እንዲያድግ መስራት፣

4. የተለያዩ የቆዳ ውጤቶችን በተለያዩ ዲዛይኖች እና በጥራት በማምረት ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር ተጠቃሚዎች ማቅረብ የሚያስችል አቅም መፍጠር፡፡

## 29. ቆዳና የቆዳ ውጤቶች አምራቾች ኃ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ተግባር

1. የተለያዩ የቆዳ ውጤቶችን በተለያየ ዲዛይን በማምረት ለተጠቃሚው ማህበረሰብ በጥራት፣ በብዛትና በተመጣጠኝ ዋጋ ማቅረብ፣
2. ለህብረት ስራ ማህበሩ አመራሮች፣ አባላትና ሰራተኞች የተቋሙን ዓላማ ከግብ ማድረስ የሚያስችሉ ስልጠናወችን እና ልምድ ልውውጦችን ማዘጋጀት፣
3. ልዩ ልዩ የቆዳ ውጤቶችን ለውጭ ገበያ በማቅረብ የገበያ ተደራሽነትን በማስፋት ተቋማዊ አቅም መፍጠር፣
4. አባላት የሚሰሯቸውን ስራዎች በአባላት ተሳትፎ መዝገብ ላይ መመዝገብ፣
5. ስለቆሻሻ አሰባሰብ አወጋገድ እና አስተዳደር ከሚመለከታቸው አጋርና ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የአመራሩንና የአባላትን አቅም መገንባት፤
6. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
7. ሌሎች የህብረት ስራ ማህበሩን ውጤታማ የሚያደርጉ ተግባራትን ያገናውናል::

## 30. የመነጽር አምራቾች ኃ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ

1. ህብረት ስራ ማህበሩ ዘመናዊ ቴክኖሎጅ በመጠቀም በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቱን ለተጠቃሚው እንዲያቀርብ ማድረግ፤
2. ምርት እና አገልግሎቶችን ጥራትና ደረጃ ለማሻሻል በመስኩ የሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲቀጠር ማድረግ ፣
3. የመነጽር አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር አባላት በዘመናዊ መንገድ የቴክኖሎጅ ሽግግር እና የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤
4. የህብረት ስራ ማህበሩ የሚያመርታቸው ምርቶች በጤና ተቋማት የታዘዙ እና ለጤና ተስማሚ የሆኑ የመነጽር ምርቶች እንዲመረቱ ማድረግ::

## 31. የመነጽር አምራቾች ኃ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ተግባር

1. ህብረት ስራ ማህበሩ በዘመናዊ ቴክኖሎጅ በመጠቀም በጥራት በማምረት በተመጣጣኝ ዋጋ የመነጽር ምርቱን ለተጠቃሚው ማቅረብ፤
2. የህብረት ስራ ማህበሩ ምርት እና አገልግሎቱን ጥራትና ደረጃ ለማሻሻል በመስኩ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማሰማራት ፣

3. አባላት ከህብረት ስራ ማህበራቸው ጋር የሚያደርጉትን ማንኛውንም እንቅስቃሴ በአባላት የተሳትፎ መዝገብ መመዝገብ፣
4. የህብረት ስራ ማህበሩ የመነጽር አሰራርን ለአባላት የቴክኖሎጅ ሽግግር የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፤
5. የመነጽር አምራቾች የህብረት ስራ ማህበር ለጤና ተስማሚ የሆኑ የዓይን መነጽሮችን ማምረት፤
6. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
7. የህብረት ስራ ማኅበሩን የመነጽር አሰራር ሊያግዙ የሚያስችሉ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ማከናወን::

## 32. <u>የልብስ ስፌት ኃ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. የህብረት ስራ ማህበሩ የልብስ ስፌት ውጤቶችን በተጠቃሚው ምርጫ እና ፍላጎት መሰረት እንዲዘጋጅ ማድርግ፤
2. የህብረት ስራ ማህበሩ የአባላትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮችን ማቃለል፤
3. የህብረት ስራ ማህበሩ ጥራት ያለቸውን የልብስ ስፌት ውጤቶች ለማህበረሰቡ ማቅረብ፣
4. የህብረት ስራ ማህበሩ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ከአቻ አገልግሎች ሰጪዎች የተሻለ ሆኖ እንዲወጣ ማድረግ፣
5. የህብረት ስራ ማህበሩ የሚያዘጋጃቸውን የልብስ ስፌት ውጤቶች ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ::

## 33. <u>የልብስ ስፌት ኃ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. የልብስ ስፌት ውጤቶች ለማህበረሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ መስራት
2. የአባላትን የልብስ ስፌት ውጤት እና አገልግሎቶችን በጥራት፤በተመጣጣኝ ዋጋ እና በበቂ መጠን ለተጠቃሚ ማቅረብ፤
3. የህብረት ስራ ማህበሩ ለህብረተሰቡ ስለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ግንዛቤ በመፍጠር በሙያው ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት፤
4. ለህብረት ስራ ማህበሩ አባላት፣ ኮሚቴዎች እና ለቅጥር ሰራተኞች ተከታታይነት ያለው ስልጠና መስጠት፤
5. የህብረት ስራ ማህበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት ከአጋር አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፣

6. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
7. የአባላትን ተሳትፎ ለማጎልበት የስራ ውጤታቸውንና ተሳትፎአቸውን መመዝገብ፣
8. የህብረት ስራ ማህበሩ ተወዳዳሪነቱን ለማሳደግና ውጤታማነትን ለመጨመር ለአባላት የዲዛይን የቅድ ስራ የተግባር ስልጠና መስጠት::

## 34. የቆሻሻ ማንሳት አገልግሎት ኃላ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ

1. የከተማ አስተዳደሩን ንጽህና ማሻሻል የሚያስችሉ የቆሻሻ ማንሳት ስራዎች እንዲሰሩ ያደረጋል፣
2. የተለያዩ ቆሻሻዎችን በአግባቡ በመሰብሰብ እና በአይነት በአይነታቸው በመለየት መልሶ ጥቅም ላይ የሚውሉበት አሰራር እንዲኖር ይሰራል፣
3. የተለያዩ ቆሻሻዎችን በብዛትና በተመጣጣኝ ክፍያ በመሰብሰብና በማስወገድ የአባላት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር እንዲቃላል ይሰራል፡፡

## 35. የቆሻሻ ማንሳት አገልግሎት ኃላ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ተግባር

1. የከተማውን ጽዳት እና ውበት የሚያሻሽሉ የአካባቢ ስራዎች ላይ መሳተፍ፣
2. የአባላትን ገቢ በሚያሳድጉ የተለያዩ ቆሻሻን የማስወገድ ስራዎች ላየ መስራት፣
3. ህብረት ስራ ማህበሩ የሰበሰባቸውን የተለያዩ ቆሻሻዎች መልሰው ጥቅም ላይ የሚወሉበትን አሰራር ተግባራዊ ያደርጋል፣ ጥቅም ላይ ለሚያውሉ አካላት ያቀርባል፣
4. የህብረት ስራ ማህበሩን አሰራር የሚያሻሽሉ የተለያዩ የአሰራር ስልቶችን ያዘጋጃሉ ፣ይተገብራሉ፣
5. አባላት የሚሰሯቸውን ስራዎች በተከታታይ በአባላት የተሳትፎ መዝገብ ላይ ይመዘግባሉ፣
6. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
7. ሌሎች የህብረት ስራ ማህበሩን ዓላማ ማሳካት የሚያስችሉ ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናሉ::

## 36. የመኪና እጥበት አገልግሎት ኃ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ

1. ህብረት ስራ ማህበሩ የመኪና እጥበት አገልግሎትን በዘመናዊ መንገድ ለህብረተሰቡ በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲሰጥ ማድረግ፤
2. የህብረት ስራ ማህበሩ የአባላትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር ለማቃለል ይሰራል፣
3. ጥራቱን የጠበቀ የመኪና ዕጥበት አገልግሎት በመስጠት ለህብረተሰቡ ጤና መጠበቅ አስተዋጽኦ ማበርከት::

37. <u>የመኪና እጥበት አገልግሎት ኃ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. ህብረት ስራ ማህበሩ የመኪና እጥበት አገልግሎት ለማህበረሰቡ በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ መስጠት፤
2. የህብረት ስራ ማህበሩ የመኪና እጥበት አገልግሎት በመስጠት የአባላትን ገቢ ማሳደግና የማህበረሰቡን ጤና መጠበቅ፣
3. ለአባሎቻቸው የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፤
4. አባላት ከህብረት ስራ ማህበራቸው ጋር የሚያደርጉትን ማንኛውንም እንቅስቃሴ በአባላት የተሳትፎ መዝገብ ላይ መመዝገብ፤
5. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
6. የህብረት ስራ ማኅበሩን ዓላማ ለማሳካት ከሚያስችሉ ሌሎች ማህበራትና ከአጋር አካላት ጋር በተቀናጀ መልኩ ተግባራትን ያከናውናል::

38. <u>የቤትና የግቢ ፅዳት አገልግሎት ኃላ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. ለነዋሪው ማህበረሰብ ውብ ቤት እና ማራኪ ግቢ እንዲኖራቸው ይሰራል፤
2. የቤትና የግቢ ጽዳትን በመጠበቅ የማህብረሰቡ ጤና እንዲሻሻል ማድረግ፡፡

39. <u>የቤትና የግቢ ፅዳት አገልግሎት ኃላ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. ለአገልግሎት ፈላጊዎች ፅዱ እና ማራኪ ግቢ እንዲሆን መስራት፤
2. የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ቤትን ማስዋብ፣
3. ለጤና ተስማሚ የሆነ የማፅዳት አገልግሎት መስጠት
4. በሚሰጡት የቤትና የግቢ ፅዳት አገልግሎት የአባላትን ገቢ ማሳደግ፤
5. አገልግሎቱን በተመጣጣኝ ክፍያ መስጠት፣
6. የአባላትን ተሳትፎ በተሳትፎ መዝገብ ላይ መመዝግብ፣
7. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
8. የህብረት ስራ ማህበሩን ዓላማ ለማሳደግ የሚያስችሉ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን፡፡

40. <u>የጽዳትና የሻወር አገልግሎት ሰጭ የህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. ህብረት ስራ ማህበሩ የጽዳትና የሻወር አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ በመስጠት የህብረተሰቡን ጤናማነት ለማጎልበት ይሰራል፣
2. የአባላትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮችን ያቃልላል፤
3. የህብረት ስራ ማህበሩ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ከአቻ አገልግሎት ሰጪዎች የተሻለ ሆኖ እንዲወጣ ማድረግ፣

4. የጽዳትና የሻወር አገልግሎት ሰጭ ህብረት ስራ ማህበር ለነዋሪው ምቹ ሁኔታ መፍጠር፡፡

41. <u>የጽዳትና የሻወር አገልግሎት ሰጭ የህብረት ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. የፀዳትና የሻወር አገልግሎት ሰጭ ህብረት ስራ ማህበር ለማህበረሰቡ በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ አገልግሎት ይሰጣል፣
2. ጤናማ ህብረተሰብ ለመፍጠር መስራት፤
3. የፀዳትና የሻወር አገልግሎት በመስጠት የአባላትን ገቢ ማሳደግ፣
4. የጽዳትና የሻወር አገልግሎት ሰጭ ህብረት ስራ ማህበር ለአባሎቻቸው የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፣
5. የጽዳትና የሻወር አገልግሎት ሰጭ ህብረት ስራ ማህበር አባላት የሚያደርጉትን ማንኛውንም እንቅስቃሴ በአባላት የተሳትፎ መዝገብ ላይ መመዝገብ ፣
6. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
7. የህብረት ስራ ማኅበሩን ዓላማ ለማሳካት ከሚያስችሉ ሌሎች የጽዳትና የሻወር አገልግሎት ሰጭ ማህበራት ጋር የተቀናጀ ተግባራትን ማከናወን፡፡

44. <u>የባልትና ውጤቶች አምራች ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. የተለያዩ የባልትና ውጤቶችን በማዘጋጀት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ፣
2. የህብረት ስራ ማህበሩ በምርቶቹ ላይ ዕሴት በመጨመር ገበያውን በማስፋፋት የአባላትን ተጠቃሚነት ማጎልበት፣
3. የህብረት ስራ ማህበሩ ደረጃውን የጠበቀ የባልትና ውጤት በማዘጋጀት ለውጭ ገበያ በማቅረብ በአገር ኢኮኖሚ ላይ አስተዋጽኦ ማበርከት፡፡

45. <u>የባልትና ውጤቶች አምራች ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. ህብረት ስራ ማህበሩ የባልትና ውጤቶችን በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚው ማቅረብ፤
2. የህብረት ስራ ማህበሩ የባልትና ውጤቶች ላይ እሴት በመጨመር ለገበያ ማቅረብ፣
3. ህብረት ስራ ማህበሩ የአባሎቻቸውን ገቢ በማሳደግ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማሻሻል መስራት፣
4. የህብረት ስራ ማህበሩ ለአባላቱ በባልትና ውጤቶች አዘገጃጀትና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ስልጠና መስጠት፣

5. የህብረት ስራ ማህበሩ አባላት ከህብረት ስራ ማህበራቸው ጋር የሚያደርጉትን ማንኛውንም እንቅስቃሴ በአባላት የተሳትፎ መዝገብ ላይ የመመዝገብ ስራ ይሰራል፣
6. የምርት እና አገልግሎቶችን ጥራትና ደረጃ ለማሻሻል በመስኩ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማሰማራት ፣
7. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
8. የህብረት ስራ ማኅበሩን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ማከናወን፡፡

46.<u>የምግብ ዝግጅት ኃ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. የህብረት ስራ ማህበሩ ጥራቱን የጠበቀና ለጤና ተስማሚ የሆነ ምግብ በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚው እንዲቀርብ ማድረግ፣
2. የህብረት ስራ ማህበሩ የተጠቃሚውን ፍልጎት በማጥናት ልዩ ልዩ የምግብ ዓይነቶችን አዘጋጅቶ ማቅረብ፤
3. የህብረት ስራ ማህበሩ የምግብ ዝግጅቱን ተመራጭ እንዲሆን በማድረግ የአባላትን እውቀት፣ጉልበትና ጊዜ አቀናጅቶ በመስራት የአባላትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮችን በዘላቂነት ለማቃለል ጥረት ማድረግ፡፡

47.<u>የምግብ ዝግጅት ኃ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. የህብረት ስራ ማህበሩ ለጤና ተስሚሚ የሆነ ምግብ በማዘጋጀት በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚው ማቅረብ፣
2. የህብርት ስራ ማህበሩ የምግብ አገልግሎት ፈላጊውን ሁኔታ በማጥናት አገልግሎቱን ወደ ተጠቃሚው ማድረስ ፣
3. የህብረት ስራ ማህበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት ከአጋር አካላት ጋር በመስራት በዘርፉ ተወዳዳሪ መሆን፣
4. የህብረት ስራ ማህበሩ በሚያዘጋጀው የምግብ ዝግጅት የተጠቃሚዎችን ፍልጎት መሰረት አድርጎ የሚሰራ መሆኑንና የሚያዘጋጃቸውን የምግብ ዝግጅቶች አስመልክቶ የማስተዋወቅ ስራ ማስራት፣
5. ለህብረት ስራ ማህበሩ አባላት፣ኮሚቴዎች እና ለቅጥር ሰራተኞች ተከታታይነት ያለው ትምህረትና ስልጠና መስጠት እና የምግብ ዝግጅት ስራውን በልዩ ልዩ መንገድ ማስተዋወቅ፣
6. የአባላትን የምግብ ዝግጅት ተሳትፎ ለማጎልበት በየጊዜው ተሳትፏቸውን መመዝገብ፣

7. የህብረት ስራ ማህበሩ የአባላትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችሮች ለመፍታት መስራት፤
8. የህብረት ስራ ማህበሩ የአባላትን እውቀት፣ ጉልበትና ጊዜ በመጠቀም የገቢ መጠኑን ማሳደግ፣
9. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
10. የህብረት ስራ ማኀበሩን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸውን ተግባራት ማከናወን::

48. <u>የጫኝና አውራጅ አገልግሎት ኃ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. የህብረት ስራ ማህበሩ የሚሰጣቸውን የእቃ ጭነትና የማውረድ አገልግሎት የንብረቱን ደህንነት በጠበቀ መንገድ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲከናወን ማድረግ፣
2. የህብረት ስራ ማህበሩ ልዩ ልዩ የጭነትና የማውረድ አገልግሎትን ስነ-ምግባር በተሞላው መንገድ አገልግሎቱን እንዲሰጥ ማድረግ፣
3. የህብረት ስራ ማህበሩ ለአባላት የስነ መግባር እና የክህሎት ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ፡፡

49. <u>የጫኝና አውራጅ አገልግሎት ኃ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. የህብረት ስራ ማህበሩ የተጠቃሚውን ማህበረሰብ ፍላጎት መሰረት ባደረገባ እና ስነ-ምግባር በተሞላው መንገድ የዕቃ የጭነትና የማውረድ አገልግሎት ማከናወን፤
2. የህብረት ስራ ማህበሩ የአባላትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮችን ለማቃለል መስራት፣
3. ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ጥራቱን የጠበቀ የእቃ መጫን እና የማውረድ አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ ፣ በፍጥነትና የንብረቱን ደህንነት በጠበቀ ሁኔታ መስጠት፤
4. የእቃ ጭነትና የማውረድ አገልግሎቱን በታማኝነትና በጥንቃቄ መተግበር፣
5. የአባላትን ተሳትፎ ለማጎልበት ሳያሰልሱ በተሳትፎ መዝገብ ላይ መመዝገብ፣
6. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
7. የእቃ ጭነትና የማውረድ አገልግሎቱን ለማሻሻል የተለያዩ ስልጠናዎች መስጠት፡፡

50. <u>የትራንስፖርት አገልግሎት ኃላ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. ምቹና ዘመናዊ የሆነ የትራንስፖርት አገልግሎት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ እንዲቀርብ በማድረግ የአባላትን ተጠቃሚነት ማሳደግ፣
2. በከተማችን ያለውን የትራንስፖርት ችግር ለማቃለል ጥረት ማድረግ፤

3. የትራንስፖርት ተጠቃሚውን ደህንነት የጠበቀ ፈጣን የትራንስፖርት አገልግሎት በተመጣጣኝ ክፍያ እንዲቀርብ መስራት፤
4. ህግና ደንብን የተከተለ የትራንስፖርት አገልግሎት ለተጓዡው እንዲሰጥ ማድረግ፤
5. በትራንስፖርት አጠቃቀም ዙሪያ ለተጠቃሚው ግንዛቤ መፍጠር ነዉ፡፡

51.<u>የትራንስፖርት አገልግሎት ኃላ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. ምቹና ዘመናዊ የሆነ የትራንስፖርት አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ በመስጠት የህብረተሰቡን ችግር ማቃለል፤
2. ደህንነቱ የተጠበቀ ፈጣን የሆነ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤
3. ህግና ደንብን የተከተል የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤
4. በትራንስፖርት አጠቃቀም ዙሪያ ለተጠቃሚው ግንዛቤ መፍጠር፤
5. የትራንስፖርት አገልግሎት ለህብረተሰቡ በማቅረብ የአባላትን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት እንዲሻሻል ማድረግ፤
6. የአባላትን ተሳትፎ በአግባቡ በአባላት የተሳትፎ መዝገብ መመዝገብ፤
7. ለአባላት በትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ስልጠና በመስጠት የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፤
8. የህብረት ስራ ማህበሩን ዓላማ ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

52.<u>የኤሌክትሪክ ምድጃ አምራቾች ኃላ/የተ/የህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. ለምግብ ማብሰያ እና ለተለያዩ የምድጃ አገልግሎት የሚውሉ የኤሎክትሪክ ምድጃዎችን በማምረት ለተጠቃሚው ተደራሽ እንዲሆን መስራት፤
2. የኤሌክትሪክ ሀይል ቆጣቢ የሆኑ ምድጃዎችን በማምረት ለተጠቃሚው በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ ለማህበረሰቡ እንዲቀርቡ ማድረግ፣
3. የኤሌክትሪክ ምድጃዎችን በማምረት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ በማቅረብ የአባላትን ገቢ እንዲጨምር ማድረግ አለበት፡፡

53.<u>የኤሌክትሪክ ምድጃ አምራቾች ኃላ/የተ/የህብረት ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. የምግብ ማብሰያ እና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉ ምድጃዎችን በማምረት ለተጠቃሚው እንዲደርስ መስራት፤
2. የኤሌክትሪክ ሀይል ቆጣቢ የሆኑ ምድጃዎችን ማምረት

3. የኤሌክትሪክ ምድጃዎችን በማምረት ለህብረተሰቡ በማቅረብ የአባላትን ገቢ መጨመር
4. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
5. በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ የኤሌክትሪክ ምድጃዎችን በማምረት ማቅርብ፤
6. በኤሌክትሪክ ምድጃዎች አመራረት ዙሪያ ለአባላት የተግባር ስልጠና መስጠት እንዲሁም ለህብረተሰቡ ስለምርቶች አጠቃቀም ግንዛቤ መፍጠር ነዉ፡፡

54.<u>የወተትና የወተት ተዋፅኦ አምራቾች ኃ/የተ/ህብ/ሥራ ማህበር ዓላማ</u>

1. የህብረት ሥራ ማህበሩ አባላት ወተትና የወተት ተዋፅኦዎችን በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ ማቅረብ፣
2. የህብረት ሥራ ማህበሩ የአባላትን ተጠቃሚነት ማሳደግ፣
3. ለአባላት ተከታታይነት ያለው ስልጠና እንዲሁም ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት፣
4. የህብረት ሥራ ማህበሩ አዳዲ ቴክኖሎጅ በመጠቀም እሴት በመጨመር ለገበያ ማቅረብ፣

55.<u>የወተትና የወተት ተዋፅኦ አምራቾች ኃ/የተ/ህብ/ሥራ ማህበር ተግባር</u>

1. የህብረት ሥራ ማህበሩ በዘመናዊ መንገድ ወተትና የወተት ተዋጽኦዎችን በማቀነባበር ለተጠቃሚው ማቅረብ፣
2. የህብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በሚሰጡት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፣
3. ጥራትና ተፈላጊነት ያለው ምርት በማምረት በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ ማቅረብ፣
4. የህብረት ማህበረ አባላትን በወተት እና የወተት ተዋፅኦ አየያዝ እና አዘገጃጅት ዙሪያ ስልጠና መስጠት፣
5. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
6. ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸውን ተግባራት ማከናወን፡፡

56.<u>የዶሮ እርባታ ህብረት ሥራ ማህበር ዓላማ</u>

1. የህብረትሥራ ማህበሩ አባላት የተለያዩ የዶሮ ዝርያዎችን በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብ ማድረግ፣
2. የህብረት ሥራ ማህበሩ የእንቁላል ምርትን ለህብረተሰቡ ማቅረብ፣
3. የህብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በሚያቀርቡት የዶሮ ምርት ተጠቃሚነታቸውን ማጎልበት፡፡

57.<u>የዶሮ እርባታ ህብረት ሥራ ማህበር ተግባር</u>

1. ጥራት ያላቸው የሥጋና የእርባታ ዶሮዎችን ለተጠቃሚው ህብረተሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ፣
2. የእንቁላል ምርትን በበቂና በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ ማቅረብ፣
3. የህብረት ሥራ ማህበሩ ዶሮን ለምግብነት ከሚያቀርቡ ጋር በጋራ ለመስራት ትስስር መፍጠር፣
4. ለህብረት ሥራ ማህበሩ አባላት ሙያዊ ሥልጠና እንዲሁም ለተጠቃሚ ግንዛቤ መስጠት፣
5. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
6. የአባላትን ተጠቃሚነት ማሳደግ፣
7. ሌሎች የዶሮ እርባታን ሊያግዙ የሚችሉ ተግባራትን ያከናውናል::

58.<u>የጤና አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. በጤናው የአገልግሎት ዘርፍ የህብረተሰቡን ጤና ለማሻሻል የራሱን ድርሻ ይወጣል፣
2. እየጨመረ የመጣውን የህብረተሰብ የጤና አገልግሎት ፍላጎት ክፍተት ለመሙላት ይሰራል፣
3. ለአባላት በተለያዩ የጤና አጠባበቅና አጠቃላይ በጤና ስርዓቱ ላይ ሙያዊ ስልጠና ይሰጣል፣
4. የአባላትን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ያጎለብታል::

59.<u>የጤና አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ዓላማተግባር</u>

1. ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ጥራት ያለውና በተመጣጣኝ ዋጋ የጤና አገልግሎት መስጠት፣
2. ለአባላት የተለያዩ ሙያዊ ስልጠናዎችን በመስጠት የአገልግሎት ጥራትን መጨመር፣
3. ለህብረተሰቡ በጤና አጠባበቅ ዙሪያ የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ግንዛቤ መፍጠር፣
4. ለአባላትና ለተገልጋዩ ህብረተሰብ የተሻለ የጤና አገልግሎት እና የስራ አካባቢ መፍጠር፣
5. የህብረት ስራ ማህበሩ ከመንግስት ጤና ተቋማት ጋር በትብብር መስራት፣
6. የአባላትን ኢኮኖሚያዊነት ተጠቃሚነት ማሻሻል፣
7. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣

8. የህብረት ስራ ማህበሩን ዓላማ ለማሳካት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሌሎች ተግባራትን ማከናውን፡፡

60. <u>የሂሳብ ምርመራ ባለሙያዎች ኃላ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. ዘመናዊ የሂሳብ ምርመራ መሰረት በማድረግ ለአገልግሎት ፈላጊዎች በጥራትና በታማኝነት አገልግሎት ይሰጣል፣
2. አግባብ ያለው ባለስልጣን ሲፈቅድ የህብረት ስራ ማህበራትን ሂሳብ ምርምራ ማድረግ፤
3. በተመጣጠኝ ዋጋ አገልግሎት በመስጠት የተጠቃሚውን እርካታ በማሳደግ ተወዳደሪነትን ማሳደግ፣
4. ለመንግስትና ለተለያዩ ድርጅቶች የስልጠ እና የማማከር አገልግሎት በመስጠት የአባላትን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ፣
5. ለአባላት ከጊዜው ጋር የሚሄድ ሙያዊ ስልጠና በመስጠት የመፈጸም አቅማቸውን ማጎልበት፡፡

61. <u>የሂሳብ ምርመራ ባለሙያዎች ኃላ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት በጥራት፣በተመጣጣኝ ዋጋና በታማኝነት መስጠት፣
2. አግባብ ያለውን ባለስልጣን በማስፈቀድ የህብረት ስራ ማህበራትን ሂሳብ መመርመር፤
3. 
4. ዘመናዊ የሂሳብ አሰራሮችን መሰረት በማድረግ ለአባላት የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፣
5. ለተለያዩ ተቋማትና ድርጅቶች የስልጠናና የማማከር አገልግሎት መስጠት፣
6. የህብረተሰቡን ፍልጎት መሰረት ያደረገ አገልግሎት በመስጠት የተገልጋዩን እርካታ ማሳደግ፣
7. ለተለያዩ ድረጅቶች እና ተቋማት በሂሳብ ምርመራ ጥቅሙ ዙሪ ግንዛቤ መፍጠር፣
8. የአባላት የሚሰጡትን አገልግሎት በተሳትፎ መዝገብ ላይ መመዝገብ፣
9. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
10. የህብረት ስራ ማህበሩን ዓላማ የሚያጠናክሩ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

62. <u>የትምህርት እና ስልጠና ባለሙያዎች አግልግሎት ኃላ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. የትምህርት እና ስልጠና አገልግሎትን በመስጠት የአባሉን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ፣

2. በተለያዩ ዘርፎች የተሰማሩ ባለሙያዎች የተቋማቸውን ግብ ማሳካት የሚስችል ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ትምህርት ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣
3. በተለያዩ የሙያ መስኮች የስልጠና ሰነዶችን ማዘጋጀት፣
4. የትምህርት ሴክተሩበተለያዩ  የሙያ ዘርፉ የተሰማሩ የመንግስት እና የግል ባለሙያዎች በተመረጡ የሙያ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣
5. የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የሚስችል ልዩልዩ የጥናት ሰነዶችን በማዘጋጅት ለተጠቃሚ እንዲቀርብ ማድረግ፡፡

63.<u>የትምህርት እና ስልጠና ባለሙያዎች አግልግሎት ኃላ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. የትምህርት  ስልጠና አገልግሎትን ለአገልግሎት ፈላጊው ደረጀውን በጠበቀ መልኩ በተመጣጣኝ ዋጋ መስጠት፣
2. የሚቀርቡ የጥናት፣ የትምህርት እና ስልጠና ጥያቄዎችን በአፋጣኝ እና በአግባቡ መመለስ፣
3. የተለያየ የትምህርት እና ስልጠና ሰነዶችን በማዘጋጀት ለተጠቃሚው ማቅረብ፣
4. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣
5. በሚሰጠው የትምህርት እና ስልጠና ተግብር የአባላቱ ኢኮኖማዊ ተጠቃሚነቱን ማጎልበት፣
6. የአባላትን ተሳትፎ በመዝገብ ላይ መመዝገብ::

64.<u>የማማከር አግልግሎት ኃላ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. ለተለያዩ ግለሰቦች፣ቡድኖች ፣ መንግታዊ እና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት በተለያዩ ዘርፎች በተመጣጣ ዋጋ የማማከር አገልግሎት ይሰጣሉ፣
2. የህብረት ስራ ማህበሩ በተለያዩ ዘርፎች እያጋጠመ ያለውን የማማከር  አገልግሎት ችግር ለማሻሻል እንደ ዕድል በመጠቀም አቅዶ ይሰራል፣
3.  ጥራት ያለው የማማከር አገልግሎት በመስጠት  የአባላትን ተጠቃሚነት ማሳደግ፡፡

65.<u>የማማከር አግልግሎት ኃላ/የተ/ህብረት ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. የህብረት ስራ ማህበሩ ማማከር አገለግሎት ለሚፈልጎ አካላት በተመጣጣኝ  ዋጋ መስጠት፣
2. ከህብረት ስራ ማህበሩ የማማከር አገልልሎት ጥያቄ ለሚያቀረቡ በጥራት አገልግሎቱን መስጠት፣
3. አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን የስራ ባህላቸውን ማጎልበት፣

4. ለአባሎቻቸው የማማከር ስራ ላይ ሙያዊ የሆነ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፣
5. የህብረት ስራ ማህበሩ የአባላትን ተሳትፎ በመዝገብ ላይ መመዝገብ፣
6. ህብረት ስራ ማህበሩ የአባላትን ኢኮኖማዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ፡፡

68.<u>የኤክትሪክ ስራ ባለሙያዎች አገልግሎት ኃ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. የህብረት ስራ ማህበሩ የከተማውን እድገት ማእከል ያደረገ የኤሌክትሪክ ስራ አገልግሎን በአስተማማኝ ደህንነት ላይ ተመስርቶ አገልግሎቱ እንዲቀርብ ማድረግ፣
2. የህብረት ስራ ማህበሩ የተጠቃሚ ግለሰቦች እና ተቋማትን ፍልጎት መሰረት ያደረገ የውስጥ ለውስጥ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታን ሙያዊ ክህሎትን ተጠቅሞ በተመጣጣኝ ዋጋ በመስራት ተፈላጊነቱን ማሳደግ፣
3. የህብረት ስራ ማህበሩ የአባላቱን የአመለካካት፣ የእውቀትና የክህሎት ችግሮች ለማሻሻል የሚረዱ ስልጠናዎችን በየጊዜው በመስጠት የአባላቱን አቅም ማጎልበትና ተወዳዳሪ በመሆን ተደረሽነቱን ማስፋት፡፡

69.<u>የኤክትሪክ ስራ ባለሙያዎች አገልግሎት ኃ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. የህብረት ስራ ማህበሩ የከተማውን እድገትና መስፋፋት መሰረት ያደረገና ወቅቱን ያማከለ አስተማማኝ የኤሌክትሪክ ስራ አገልግሎት ማቅረብ ፣
2. የህብረት ስራ ማህበሩ የኤሌክትሪክ ስራ አገልግሎት ፈላጊዎችን ጥያቄ በጥንቃቄ፣ በጥራት በመስራት ማስተዋወቅ፣
3. የህብረት ስራ ማህበሩ ለአባላትና ለቅጥር ሰራተኞች በኤሌክትሪክ ስራ በአገልግሎት አሰጣጥና በሙያ ብቃት ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፤
4. የህብረት ስራ ማህበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት ለኤሌክትሪክ ስራ ቅርበት ካላቸውና አጋር አካላት ጋር ተባባሮ መስራት፣
5. የህብረት ስራ ማህበሩ የአባላትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ለመፍታት መጣር ፤
6. የአባላትን ተሳትፎ ለማጎልበት ባላሰለሰ መንገድ ተሳትፎቸውን መመዝገብ::

70.<u>የምህንድስና ሙያ አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. የምህንድስና ሙያ አገልግሎት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የማማከር፣ የንድፍ፣የቅየሳና የግንባታ ስራ መስራት፣
2. ጥራታቸውን የጠበቁ የምህንድስና ሙያ አገልግሎት በተመጣጣኝ ክፍያ ለኅብረተሰቡ ማቅረብ፣

3. የአባላትን ሙያዊ ብቃትና ክህሎታቸውን በየጊዜው በማሳደግ ተወዳዳሪነታቸውን ማጎልበት፡፡

71.<u>የምህንድስና ሙያ አገልግሎት ኃላ/የተ/ ህብረት ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. ለተለያዩ ግለሰቦች፣ድርጅቶችና ተቋማት የሚጠይቁትን የሙያ ክህሎት ስልጠናና የማማከር አገልግሎት መስጠት፣
2. ህብረት ስራ ማህበሩ ጥራታቸውን የጠበቁ የምህንድስና ሙያ አገልግሎቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ መስጠት፣
3. ማህበረሰቡ የሚያነሳቸውን ሙያዊ የአገልግሎት ጥያቄዎች በመመለስ የተጠቃሚውን እርካታ ማሳደግ፣
4. የህብረት ስራ ማኅበሩን ዓላማ ለማሳካት ከሚያስችሉ ሌሎች አጋር አካላት ጋር የተቀናጀ ተግባራትን ማከናወን፡፡

72.<u>የግንበኞችና አናፂዎች አገልግሎት ኃላ/የተ/ህ/ስራ ማህበር ዓላማ</u>

1. ደረጃውን የጠበቀ የግንባታ ስራ እንዲሰራ ማድረግ፤
2. የግንባታና የአናፂነት አገልግሎትን ኮንትራት በመውሰድ በተመጣጣኝ ክፍያ እንዲሰሩ ያደርጋል፤
3. የግንባታና የአናፂነት ስራን በተመለከተ የተግባር ስልጠና በመስጠት የባለሙያዎችን አቅም ማሳደግ፤
4. የግንባታ እና የህንፃ ስራዎችን ህግና ደንብን ተከትሎ ይሰራል፡፡

73.<u>የግንበኞችና አናፂዎች አገልግሎት ኃላ/የተ/ህ/ስራ ማህበር ተግባር</u>

1. ጥራቱን የጠበቀ የግንባታና የአናፂነት ስራዎችን መስራት፤
2. በተመጣጣኝ የኮንትራት ክፍያ የግንባታና አናፂነት አገልግሎት መስጠት፤
3. የተግባር ስልጠና ለባለሙያዎች በመስጠት የግንበኞችንና የአናፂዎችን ሙያ ማሻሻል፤
4. የህንፃ ግንባታ ህግና ደንብ ተከትለው የግንባታ ስራዎችን ማከናወን፡፡

74.<u>የቱሪዝም አገልግሎት ኃ/የተ/ህብ/ሥራ ማህበር ዓላማ</u>

1. ህብረት ሥራ ማህበራቱ የቱሪዝም ስራዎችን ለአገር ውስጥና ለውጭ ተጠቃሚዎች መስጠት፤
2. ህብረት ሥራ ማህበራቱ ከአጋር ህብረት ሥራ ማህበረት ጋር ልዩ፣ልዩ ባህላዊ ጌጣጌጦችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ ማቅረብ፤

3. የአገሪቱን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ከመንግስት ጋር በመተባበር ማስተዋወቅ፤
4. ለህብረት ስራ ማህበር አባላት በዘርፉ ስልጠና እንዲሁም ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት፤
5. የህብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ተጠቃሚነት ማጉላት፡፡

75.<u>የቱሪዝም አገልግሎት ኃ/የተ/ህብ/ሥራ ማህበር ተግባር</u>

1. የአገር ውስጥ የቱሪዝም አገልግሎትን ለአገር ውስጥና ለውጭ ጎብኝዎች በተመጣጣኝ ዋጋ መስጠት፤
2. ልዩ፣ልዩ ባህላዊ ጌጣጌጦችን ከሌሎች ህብረት ስራ ማህበራት ጋር በመተባበር በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚ ማቅረብ፤
3. የቱሪዝሙን እንቅስቃሴ ከመንግስት ጋር በመተባበር የማጉላት ስራ መስራት፤
4. ለአባላት ተከታታይነት ያለው ስልጠና እንዲሁም ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት፣
5. የቱሪዝም እንቅስቃሴውን በማስፋት የአባላትን ተጠቃሚነት ማጉላት፡፡

76.<u>መነሻ ካፒታል</u>

1. ማንኛውም መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበር ሲቋቋም በሚያቀርበው የስራ እቅድና የአዋጭነት ጥናት መሰረት ቢያንስ የመጀመሪያ ዓመት የስራ ማስኬጃ ወጭዎቹን መሸፈን የሚችል ካፒታል ይዞ መመስረት አለበት፤
2. የህብረት ስራ ማህበራት የህብረት ስራ ዩኒዩንን ለመመስረት መስራች መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት በአዋጭነት ጥናት መሰረት እቅዳቸውን ለመፈፀም የሚያስችል በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ መሰረት ቢያንስ የጠቅላላ ካፒታላቸውን ሀያ አምስት ፐርሰንት (25%) ያህል ዕጣ መግዛት ሲችሉ ነው፤
3. የህብረት ስራ ማህበራት ፌደሬሽን ሊመሰረት የሚችለው በተደረገው የአዋጭነት ጥናት መሰረት እቅዳቸውን ለመፈፀም እንዲያስችል በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ መሰረት አባል ህብረት ስራ ማህበራት ዩኒዩኖች ቢያንስ የጠቅላላ ካፒታላቸውን ሰላሰ ፐርሰንት (30%) ያህል ዕጣ መግዛት ሲችሉ ነው፡፡

77.<u>የብቃት ምዘናና ደረጃ እውቅና አሰጣጥ</u>

1. የህብረት ስራ ማህበራት የመመዘን ጥያቄ በጽሁፍ አግባብ ላለው ባለስልጣን ማቅረብ አለባቸው፤

2. የህብረት ስራ ማህበራት በየሶስት ዓመቱ የመመዘን ግዴታ ሲኖርባቸው አግባብ ያለው ባለስልጣንም ለተመዘኑት ህብረት ስራ ማህበራት የብቃት ደረጃ እውቅና የምስክር ወረቀቱን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚሰጥ ሆኖ የብቀት ምዘና ውጤቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ውሳኔ ማግኘት ይኖርበታል፤
3. የህብረት ስራ ማህበራት የምስክረ ወረቀቱን በሚታይ ቦታ የማስቀመጥ እና ሲጠየቁም የማሳየት ግዴታ አለባቸው፤
4. የህብረት ስራ ማህበራት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስመዘን ጥያቄ ካላቀረበ እና ካላስመዘነ አግባብ ያለው ባለስልጣን ኅብረት ሥራ ማህበራቱን የምዝገባ ወረቀቱ አይታደስላቸውም፤
5. ዝርዝር አፈጻጸሙ በህብረት ስራ ማህበራት የብቃት ምዘናና ደረጃ ማረጋገጥ መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 78.ስምና መለያ ምልክት

1. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራት የራሱ የሆነ መጠሪያ ስም እና ልዩ ምልክት ሊኖረው ይገባል፤
2. አንድ ኅብረት ሥራ ማኅበር በተመዘገበበት ስም እና ምልክት ሌላ ተመሳሳይ ዓላማ እና ተግባር የሚያከናውን የኅብረት ሥራ ማኅበር ሊመዘገብ ወይም ሊጠቀምበት አይችልም፡፡

## 79.አባል ለመሆን የሚያበቁ ሁኔታዎች

የሚከተሉትን የሚያሟላ ግለሰብ  የኅብረት ሥራ ማኅበር አባል መሆን ይችላል፡-

1. አባሉ ነዋሪነቱ ወይም ሥራው በህብረት ስራ ማኅበሩ የሥራ ክልል የሆነ፣
2. ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፣
3. የህብረት ስራ ማህበሩ እጣ ለመግዛት እና የመመዝገቢያ ክፍያ መክፈል የሚችል፤
4. የህብረት ስራ ምህበሩን እጣ ለመግዛት እና የመመዝገቢያ ክፍያ ለመክፈል የሚችል፤
5. የህብረት ስራ ማህበሩን ዓላማ እና መተዳደሪያ ደንብ የተቀበለና ግዴታዎችን ለመፈፀም ፍቃደኛ የሆነ፤
6. አባልነቱ መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት እና ከመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት በላይ ከሆነ አግባብ ባለው ባለስልጣን ተመዝግቦ ህጋዊ ሰውነት ያገኘ መሆን አለበት፤
7. በሌላ ተመሳሳይ  ህብረት ስራ ማኅበር አባል ያልሆነ ወይም በተመሳሳይ ተግባር በሚያከናውን የህብረት ስራ ማህበር ላይ፣

8. አንድ የህብረት ስራ ማህበር ካዘገጀው እጣ በመተዳደሪያው ደንቡ መሰረት አንድ አባል መግዛት ያለበትን እጣ መግዛት የሚችል እና የመመዝገቢያ ክፍያ መክፈል የሚችል፤
9. በህግ መብቱ ያልተከለከለ፣

80.<u>አባል ለመሆን የሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1. አባል ለመሆን የሚፈልግ ሰው የህብረት ስራ ማኅበሩ ያዘጋጀውን የአባልነት ማመልከቻ ቅፅ ሞልቶ ያቀርባል፣
2. የሥራ አመራር ኮሚቴው የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ መቀበሉን ወይም አለመቀበሉን በመተዳደሪያ ደንቡ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ለአመልካቹ ያሳውቃል፣
3. አመልካቹ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው ለጠቅላላ ጉባዔ በፅሑፍ ይግባኝ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

81.<u>የአባላት መብትና ግዴታ</u>

1. የአንድ ኅብረት ስራ ማህበር ህልውና እና ዕድገት ቀጣይነት የሚወሰነው በአባላት መብትና ግዴታ መካከል ያለው ሚዛን በአግባቡ የተጠበቀ ሲሆን ነው ፤
2. የህብረት ስራ ማህበሩ ለአባላት የሚሰጠውን ማንኛውንም አገልግሎትና ጥቅም ፍትሐዊ በሆነ መልኩ የማግኘት፣
3. አባላት በዲሞክራሲያዊ መንገድ በሁሉም የህብርት ስራ ማኅበሩ ጉዳዮች ላይ የመሳተፍ፤
4. በስብሰባዎች ላይ ሃሣብ የመስጠት፤
5. በሌላ በኩል ደግሞ መብትን በተሟላ መንገድ ለመጠቀም ግዴታውንም መወጣት አለበት፡፡

82.<u>የህብረት ስራ ማህበራት የአባላት መብት</u>

ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፣

1. ማናኛውም አባል ወይም ተወካዩ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት በተሳትፎው መጠን ህብረት ስራ ማህበሩ የሚሰጠውን አገልግሎትና ጥቅም የማገኘት መብት፣
2. አባሉ ወይም ተወካዩ በህብረት ስራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በመገኘት የመምርጥና የመመረጥ እንዲሁም ድምጽ የመስጠት መብት፣
3. ማንኛውም አባል መብቶቹና ጥቅሞቹ ተከብረውለት በጥያቄው መሠረት ከህብረት ስራ ማህበሩ ከአባልነት የመሰናበት መብት፣

4. ማንኛውም አባል ስለ ህብረት ስራ ማህበሩ እንቅስቃሴ መረጃ የማግኘት መብት አለው፤
5. ህብረት ስራ ማኅበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በማንኛውንም ሰዓት ጥያቄና ቅሬታ የማቅረብ፣አስተያየት የመስጠትና መልስ የማግኘት መብት፡፡

83.<u>የአባላት ግዴታ</u>

1. አባሉ የህብረት ስራ ማህበሩን መተዳዳሪያ ደንብ፣መመሪያዎችንና የጠቅላላ ጉባኤ የውሳኔዎችን የማክበር፣
2. አባሉ የሚሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ የመወጣት እና በጋራ የሚሰሩ ሥራዎችን የማከናወን፣
3. ማንኛውም አባላል በህብረት ስራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚሰጠውን ስራዎችን የመስራት፣
4. የህብረት ስራ ማህበሩ አባል የህብረት ስራ ማህበሩን ንብርት የመጠበቅና የመንከባከብ ፣
5. አባላት ከህብረት ስራ ማህበሩ የግብይት ተሳትፎ የማድረግ፣
6. ማናኛውም አባል በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት እንዲሸጥ የታወጀው የዕጣ መጠን ተሽጦ ሲጠናቀቅ የህብርት ስራ ማህበሩ ተጨማሪ ካፒታል ካስፈለገው አባሉ የመግዛት ግዴታ አለበት፤
7. የህብረት ስራ ማህበሩ ቀደም ሲል በአባል ተይዞ የነበረ እጣ በአራት አመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልተሸጠ ለጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ እንዲቀርብ ይደረጋል፣
8. የማንኛውም መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበር አባል በጠቅላላ ጉባኤ ተወስኖ ከተሸጠው የዕጣ መጠን 10% በላይ የመግዛት ድርሻ ሊኖረው አይችልም፤
9. የማንኛውም ህብረት ስራ ዩኒዬን ወይም ፌዴሬሽን አባል በጠቅላላ ጉባኤ እንዲሸጥ ከተወሰነው የዕጣ መጠን 50% በላይ የመግዛት ድርሻ ሊኖረው አይችልም፡፡

84.<u>ከአባልነት ስለመሰናበት እና ስለመመለስ</u>

1. **ከአባልነት የሚያሰናብቱ ዋና ዋና ምክናያቶች፡-**
   ሀ) የህብረት ስራ ማህበር አባል በራሱ ፈቃድ ሲለቅ፣
   ለ) የህብረት ስራ ማህበር አባል ከተደራጀበት የስራ ቦታ ወይም የመኖሪያ አካባቢን ለቆ ሲሄድ፤

ሐ) የህብረት ስራ ማህበሩ አባል ሲሞት ወይም የህብረት ስራ ማህበሩ ሲፈርስ መ. የህብረት ስራ ማህበሩ አባል የሚሰጠውን ኃላፊነት ተቀብሎ ለመስራት ፈቃደኛ ካላሆነ ፣

ሠ) የህብረት ስራ ማህበር አባል ማህበሩ የሚሰጠውን ኃላፊነት ፍትሐዊ ባልሆነ መንገድ ያለ አግባብ ተጠቅሞ ሲገኝ፣

ረ) የህብረት ስራ ማህበሩ አባል በጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ ያለ ፈቃድ ሦስት ጊዜ ከቀረ፣

ሰ) የህብረት ስራ ማህበሩን ከተቋቋመበት አላማ ውጪ ሲጠቀምበት ከተገኘ፣

ሸ) የህብረት ስራ ማህበሩ ያወጀውን ዕጣ ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ከፍሎ ያላጠናቀቀ፣

ቀ) የህብረት ስረ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ እና ሌሎች ልዩ ልዩ መመሪያ ባለማክበር ናቸዉ፡፡

2. **የተሰናበተ አባል ወደ ማህበሩ እንዲመለስ የሚያደርጉ ምክንያቶች፡-**

ሀ) አባሉ በጥፋተኝነቱ ተጸጽቶ ማህበሩን በደብዳቤ የይቅርታ ማመልከቻ በማስገባት ከጠየቀና ይህም በጠቅላላ ጉባኤ ተቀባይነት ካተገኘ፣

ለ) አባሉ በራሱ ፈቃድ ከተሰባበተ በኋላ በተቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት ሊመለስ ይችላል፣

ሐ) አባሉ ግዴታውን ባለመወጣቱ ከአባልነት የተሰናበተ አባል ጥያቄ ካቀረበ ከአንድ በጀት ዓመት በኃላ በጠቅላላ ጉባኤ በሚወሰነው መሰረት ሊመለስ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስለህብረት ስራ ማህበራት መተዳደሪያ ደንብ</u>

85.<u>*የመተዳደሪያ ደንቡ ይዘት*</u>

1. የህብረት ስራ ማኅበሩ ሥም አድራሻ እና የሥራ ክልል ፣
2. የህብረት ስራ ማህበሩ ራዕይና ተልዕኮ፣
3. የህብረት ስራ ማኅበሩ ዓላማና ተግባር፣
4. የኀብረት ሥራ ማኅበራት ዕሴቶችና መርሆዎች፣
5. የህብረት ስራ ማህበሩአባል ለመሆን የሚያበቁ መመዘኛዎች፣
6. የህብረት ስራ ማህበሩ የመመዝገቢያ እና የዕጣ ክፍያ፣

7. የህብረት ስራ ማህበሩ የአባልነት ማመልከቻ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ፣
8. የህብረት ስራ ማህበሩ የአባላት መብትና ግዴታ፣
9. የህብረት ስራ ማህበሩ የአባልነት መቋረጥና የክፍያ አፈፃፀም፣
10. የህብረት ስራ ማህበሩ ስብሰባ አጠራር፣ምርጫና ድምፅ አሰጣጥ፣
11. የህብረት ስራ ማህበሩ ኮሚቴ አባል ለመሆን የሚያበቁ መመዘኛዎች፣
12. የህብረት ስራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሁኔታ፣
